# እጀታ!




በሰዶም ኃጥያት ተጠምቀህ በይሁዳ እጆች ተጣመህ፣
ግንድና ሥርን በመክዳት ተምሳር ቅርቃር ተሸጠህ፣
ስንቱን ቀጥ ያለ የዛፍ ዘር ቆርጦ በመጣል ያስፈጀህ፣
ያለፈው አልበቃ ብሎ ዛሬም ተፋሶች ተጣበክ፡፡

ስለት ባናትህ ሰክተህ ጫካና ዱሩን ጨፍጭፈህ፣
በውስጥ የሚኖሩትን አንበሶች ለጥቃት ጉዳት አጋልጠህ፣
በሜዳ አህያ ከርከሮ አገሩን ምድሩን አስወረርክ፡፡

በራስህ መንፈስ አታዝዝ አትጓዝ በገዛ እግሮችህ፣
ጅራትህን ተእጆች ለጥፈህ ኩንቢህን ተምሳር ቅርቃር ወትፈህ፣
ዛሬም የዛፎችን ዘር ልታስፈጅ እንደ ትል ትወራጫለህ፡፡

እንደ አሽከር ሁሌ መታዘዝ የሎሌ ኑሮ ሳይቀፍህ፣
ግንድህ ተቆርጦ ማለቁ ተምድር መጥፋት ሳይቆጪህ፣
ትቢያ አመድ ሆነህ ታርፋለህ ተምድጃ ተእሳት ተጥለህ፣
የማታ ማታ ምሳሩ ገዝግዞ ቅልጥም አድርጎ ሲሰብርህ፣
ስኳር ላሹን ሰው ጠይቀው ይኸንን መልዕክት ታላመንክ፡፡

በተረገመው ተፈጥሮህ ባልተባረከው ምግባርህ፣
እንደ ሳጥናኤል ይሁዳ ስለት ብዕሮች ሲወጉህ፣
ታሪክ በመዛግብቱ ትውልድ በቅየው ሲወቅስህ፣
ምድር ተምድጃ ስጠብስህ ሰማይ ሲኦል ውስጥ ሲያነድህ፣
ጠማማው እንጨት እጀታ እስከ ዘላለም ይወሳል ውርደትህ፣
የአምስቱን ዘመን ባንዳዎች ቀፋፊ ታሪክ አንብ ታላመንክ፡፡

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ሰኔ ሁለት ሺ አስራ ሶስት ዓ.ም.